Association of Ethiopians in Europe
info@ethiodiaspora.net www.ethiodiaspora.net

## Statement of condemnation against atrocities, genocide that has been committed on Amhara people by the present regime in Ethiopia.

ግንቦት 18 ቀን 2014 ዓመተ ምህረት - May 26, 2022

እኛ በ16 የአውሮፓ ሃገራት ዉስጥና የምንገኘ ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያን ከዚህ የሚከተለዉን የአቋም መግለጫ አዉጥተናል ::

United kIngdom, Ireland, Spain, Netherlands, Germany, Spain, Finland, Norway, Belgium, Switzerland, Italy, Sweden, Denmark, Luxemburg, France, Austria

ጉዳዩ; በኢትዮጵያ ስልጣን የተፈናጠጠው ራሱን የኦህዴድ /ኦነግ ብልፅግና መንግስት ነኝ ብሎ የሚጠራው፣ በተለይ ፣-

በአማራ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ አነጣጥሮ ፣ የአማራን ዘሩን እያጠፋ፣ እያሰረና እያፈናቀለ አጠናክሮ ስለቀጠለ ፣

ይህንን አለም አቀፍ የወንጀል ድርጊቱን ለማውገዝ፣ በአስቸኳይ እንዲያቆምና የአማራን ህዝብ ተፈጥሮአዊ ፣ ሰብአዊና ህጋዊ መብቱን እንዲያከብር ለማስጠንቀቅ ነው።

እኛ በአውሮፓ የምንኖር የአማራ ነገድና ከተለያዩ ነገዶች የተውጣጣን ቅልቅል ኢትዮጵያውያን ፣

በሀገራችን ውስጥ እየተካሄደ ያለውንና ለከት ያጣ መንግስታዊ ሽብርተኝነትና ፋሽሽታዊ ዘረኝነት ፣ በጽኑ እናወግዛለን-

የአማራውን ሕዝብ ራስን የመከላከልን ህጋዊ እርምጃ እንደግፋለን- ለመላው ዲያስፖራ ጥሪም እናስተላልፋለን።

ዛሬ በሀገራችን ኢትዮጲያ በተለይም የአማራው ኢትዮጵያዊ በብዛት በሚኖርበት ርስቱ፣ በጎጃም፣ በወሎ፣ በሸዋና በበጌ ምድር/ጎንደር፣ በኢትዮጵያ ዋና ከተማችን በአዲስ አበባ ፣ በተከፈተ መንግስታዊ ሽብርተኝነት በርካታ ንጹኃን በግፍ እየታፈኑ፣ እየተገደሉ፣ መሬታቸው እየተወረረ ቀጥሏል።

ለማስረጃ ያህል ከብዙው በጥቂቱ፣ ግንቦት10 ቀን 2014 ዓ .ም በጎጃም ክፍለ ሀገር፣ በመርዓዊና ሞጣ አካባቢዎች ና በወሎ ክፍለሀገር፣ በወልዲያ ከተማ፣ መንግስታዊው ሽብርተኛ አፋኝ ቡድኑ፣ በከፈተው ተኩስ፣ በመራዊ 17 በወልዲያ 3 ንጹሃን መገደላቸውን እና በርካቶች መቁሰላቸውን በየአካባቢዎቹ ካሉ ሆስፒታሎችና ከሰለባዎች ቤተሰቦች ለመረዳት ተችሏል።

ይህ ፋሽሽታዊ የዘረኛ ስርአት፣ ድርጊቱ ተራ፣ ሕገ ወጥነትን የተላበሰ ብቻ ሳይሆን;

የተባበሩት መንግስታት የደነገጋቸውን አለም አቀፍ ህግን፣ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችንና፣ ማንኛውም ዜጋ በሀገሩ፣ በህይወት የመኖርና አጠቃላይ ደህንነቱ መጠበቅ እንደሚገባው ያሰፈራሳቸውን መብቶችን የገፈፈ፣ አለም አቀፍ ወንጀል ነው።

ስለሆነም፣ ማሕበራችን መላው የአማራ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ መላው የኢትዮጱያ ሕዝብን፣ ከወገኑ የአማራ ሕዝብ ጎን ቆሞ፣ በመላው ኢትዮጲያ ሁለንተናዊ የነፃነትና የህልውና ትግል እንዲከፍት ጥሪውንም ያስተላልፋል። በተለይም መላው የአማራ ሕዝብ ዛሬ በጎጃምና በወሎ ሕዝብና ፋኖ

ላይ  የተከፈተውን የዚህ ዘር አጥፊ ቡድን  የጎንደርና  የሸዋ አማራ በፍጥነት ለህልውናው እንዲነሳ ማሳሰብ እንወዳለን።

 በዚሁ አጋጣሚ በመላው ዓለም የሚገኝ የኢትዮጲያ ዳያስፖራ፣ በተለይም፣  በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓና በተቀረው ዓለም ያላችሁ በሙሉ፣  በአስቸኳይ፣  ዓለም አቀፍ የሕዝባችንን ትግል ድጋፍና የመንግስታዊው ሽብርተኝነትን የማውገዝ ተከታታይ ሰልፍ እንድናካሂድ በአክብሮት  እናሳስባለን።

## ውድ የኢትዮጲያ ሕዝብ ሆይ፡-

## ፋሺስታዊውና ዘረኛ ቡድን ዛሬ በሀገራችን ውስጥ በከፈተው ዘመቻ፣ በርካታ ንጹሃንን እያፈነ በማሰር አንዳንዶቹን ደብዛ እያጠፋም ነው።

## የሀገር ባለውለታውን፣  ብ/ጀነራል ተፈራ ማሞን አፍኖ በማሰር፣ ጋዜጠኞች፣ ፖለቲከኞችን፣ የማሕበረሰብ አንቂዎችንና ገበሬዎችን መግደልና ማፈናቀል ቀጥሏል።

እንደነ ጋዜጠኛ ሰለሞን ሹምዬ ጋዜጠኛና ታሪክ ጸሀፊ ታዲዮስ ታንቱ፣ መሰከረም አበራ ፣  የአሻራ ሚዲያና የንስር ብሮድካስቲንግ ሚዲያ አባላትን ጨምሮ፣  እነ ቲና በላይና በርካቶችን እያፈነ አስሯል።

ይህንን ግልፅ ምን ታመጣላችሁ የእብሪት ጦርነት፣ እኛ በአውሮፓ የምንኖር ኢትዮጲያዊያን፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሀገሩ በነፃንት፣ በፍትህና እኩልነት የመኖር መብቱ እስኪመለስና  እስኪሲረጋገጥ ድረስ፣ ከህዝባችን ጎን ቆመን ዘርፈ ብዙ ድጋፍና ትግላችንን እንቀጥላለን።

ይህ ፋሽሽታዊ በድን በአማራ ህዝብ ላይ ያሰማራቸውን የኦሮሞ ነገድ አፋኝ ቡድን በአስችኳይ የአማራ ክልል ብለው ዘረኞች ከከለሉት እንዲያስወጣ በከፍተኛ ቁጣ እናስጠነቅቃለን።  ድርጊቱን በጽኑ አቋም እንኮንናለን-

በአንጻሩም የትኛውንም የሕዝባችንን እራስን የመከላከል ትግልን  ሙሉ በሙሉ የምንደግፍና ከሕዝባችን ጎን የምንቆም መሆናችንን እየገለጽን ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ያሰራቸውን ሁሉ ዜጎች በአስቸኳይ እንዲፈታና ብሎም በአማራ ክልል ያሰማራቸውን ኦነጋዊ የኦህዴድ ሰራዊትን በአስቸኳይ እንዲያስወጣ እንጠይቃለን።

የተቀረው ኢትዮጲያዊ ወገናችን በተለይ በዲያስፖራ ያለው በሙሉ ከሕዝቡ ጎን እንዲቆምና ይህንንም አቋሙን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚያካሂደው ሰልፍ እንዲገልጽ በአክብሮት እንጠይቃለን - ደግመን ጥሪም እናቀርባለን።

የአማራን ሕዝብ እራስን የመከላከልን እርምጃ ሙሉ በሙሉ እንደግፋለን !!! እውነትና ሕዝብ ያሸንፋል-!!

ኢትዮጵያ ሀገረ- እግዚአብሔር፣  በፈጣሪያችን ሀይል፣ና በአማኝ ህዝቧ ተከብራ ለዘልዓለም ትቀጥላለች!

የኢትዮጵያዉያን ማህበር በአውሮፓ

www.ethiodiapsora.net